# ክትግራይ ማሕበረ ሰብ በዳላስና አከባቢው የተሰጠ መግለጫ

ትግራይ ኦንላይን August 31, 2016

በዳላስ ፎርትዎርዝ አካባቢ የምንኖር የትግራይ ተወላጆች አገስት 21,2016 የትግራይ መረዳጃ ማህበር በጠራው ህዝባዊ ስብሰባ በመገናኘት በአገራችን ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በመወያየት የሚከተሉትን ባለ ዘጠኝ ነጥቦች የአቋም መግለጫ አስተላልፈናል ፥፥

1. በጎንደር ና አካባቢው ህይወታቸው ባለፈው ንብረታቸው የወደመባቸው ወገኖቻችን በሙሉ ጥልቅ ሀዘናችን ፤ንገልፃለን
2. በኦሮምያ ና በአማራ ክልል በተፈጠረው አለመረጋጋት ህይወታቸው ላጡ ወገኖቻችን ጥልቅ ሀዘናችን እንገልፃለን
3. በትግራይ ተወላጆች ያነጣጠረ የዘረኝነትና የጥላቻ ጥቃት እንዲቆም የአማራ ክልል መንግስት ወንጀለኞችን ወደ ህግ እንዲያቀርብ እንጠይቃልን
4. የትግራይ ህዝብ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ የመሰለውን የመደገፍና የመቃወም ህገመንግስታዊ መብቱ ይጠበቅ
5. የፀጥታ ሀይሎች ከመጠን በላይ ያለፈ እርምጃ እንዳይወስዱ በቂ ስልጠናና ትጥቅ እንዲኖራቸው ይደረግ፥ እስካሁን ከመጠን ያለፈ የተወሰደ እርምጃ ካለ በአስቾኳይ ይጣራ ዘንድ እንጠይቃለን
6. የብዙሀን መገናኛ ዘዴዎች ሁሉም ወገን ያለ አድልዎ ድምፅ እንዲያሰማ በእኩልነት እንዲያገለግሉና በዘር ያተኮረ ጥላቻ ዘመቻ ያቁሙ
7. ማንኛውም ጥያቄ በህግና በህገመንግስቱ እንጂ በሀይልና በጥላቻ አይፈታም፥ በመሆኑም በ አገራችን እየተከሰተ ያለው አደጋ ለመከላከል ወላጆች ልጆቻቸውን ይምከሩ ፥ መንግስትም የህዝብ ጥያቄ በአስቾኳይ መልስ ይሰጥ ዘንድ እንጠይቃለን
8. የኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ወደ እርስ በርስ ጦርነትና ትርምስ ለማስገባት ሌት ተቀን የሚጥሩ የውጭ ሀይሎችና ተላላኪዎቻቸው መንግስት አሰፈለጊውንና ዘላቂ እርምጃ እንዲወስድ እንጠይቃለን
9. የማንኛውም የብሔር አባል በማንኛውም ሌላ ብሔር ላይ የሚያካሔደው ዘረኛና ስድብ አዘል ቅስቀሳ እናወግዛለን